

# ተነስ ፣ተነስ

*ጉብ ልበልበት ልፈናጠጥበት፣*
*ጎዞዩን ልጀምር ባስቸኳይ በፍጥነት፣*
*በምስራቅ በደቡብ፣*
*በሰሜን በምዕራብ፣*
*ልመላለስበት እኔም እንዳባቴ፣*
*ጀግንነት ከደሜ ከኢትዮጵያዊነቴ፣*
*በፍጥነት ጋልቤ ኮቴውን ልበለው፣*
*ቃታዬን ልሳበው ክንዴንም ላሳየው፣*
*ዳገት ሽንተረሩ ቁልቁለት ሳይገታኝ፣*
*አቀበት ወጥቼ ክልል ሳያግተኝ፣*
*ድንበር ሳይወስነኝ በጎሳ ሳይከፍለኝ፣*
*የእኩይ መመሪያ እምቢ አሻፈረኝ፣*
***ፈረሴን ልጫነው ዝናሬን ልታጠቅ፣***
***ያ አራሙቻ ወንበሩን እስኪለቅ፣***
*የፍቅርሽ ነበልባል ልቤን እየበላ፣*
*እንቅልፍ አሳጥቶ እኔን እያጉላላ፣*
*ግልቢያዬን ልጀምር ልምነሽነሽበት፣*
*በአራቱ ማዕዘናት አገሬን ላድናት፣*
*ኢትዮጵያ እናታችን የተወለድንባት፣*
*በደም የተሰራች በእምዬ የቆመች።*



ከፋፍሎ ከልሎ ሕዝቡን እየነዳ፣

ከጫካ እየዶለ እያሳየ እዳ፣

ፍቅርን ለሚንድ አንድነት ለሚያፈርስ፣

ሕዝቡን አስጨንቆ ስርዐት ለሚያፋልስ፣

ጥላቻ እየነዛ ዕድሜውን ለሚያድስ፣

ሕብረት የሚጠላ አንድነት ጠላቱ፣

የግራዚያኒ አሽከር ወያኔ ፋሽስቱ።

***ፈረሴን ልጫነው ዝናሬን ልታጠቅ፣***

***ያ አራሙቻ ወንበሩን እስኪለቅ፣***

ኢትዮጵያዊ ጅግና ካባቱ ያልተለየ፣

እናት ሃገር ጸንታ በቁሙ ካላየ።

እራሱ ነዶ ፋና የሚሆን፣

አደራ የሚጠብቅ የአባት የእናቱን፣

ሰላቶ ደፊ ደፋር ምስጉን።

ኢትዮጵያን አርጎ መካነብካሬ፣

ሰብዓዊነት የለው ስራው የዱር አውሬ፣

በለቅሶ ሸለቆ ጨለማ የከተተ፣

ሕጻን አዋቂውን የተጠናወተ፣

ወያኔ ቱርኪ ነው መንገዱ ሰዋራ፣

ሕዝቡን ያዋረደ ለሕጻናት ያልራራ፣

ታላቅ ሞገድ ይምጣ ማዕበል ይውሰደው፣

በሱናሚ ይመታ ቁጣ ያሰናክለው፣

እንደደራሽ ውሃ የሕዝብ እምባ ይጥረገው።

***ፈረሴን ልጫነው ዝናሬን ልታጠቅ፣***

***ያ አራሙቻ ወንበሩን እስኪለቅ፣***

**መይሳው ከምድረ ስዊድን**

**12/30/2013**